ውድ Seattle Foodservice Business፣

**ይህ ከSeattle Public Utilities (SPU) አዲስ የምግብ አገልግሎት-ዕቃ መስፈርቶች ያለው ዝማኔ ነው። የSPU የዳይሬክተሩን ደንብ SW-500 አሻሽለዋል፡- "ለምግብ አገልግሎት እቃዎች እና ማሸጊያ ምርቶች መስፈርቶች እና ጊዜያዊ ልዩ ሁኔታዎች" የተሻሻለው ህግ ከጁላይ 1፣ 2023 ጀምሮ ተግባራዊ ነበር።**

በተሻሻለው ደንብ መሰረት፡-

- ሁሉም የምግብ አገልግሎት እቃዎች በጊዜያዊነት ከሚፈቀድላቸው የተወሰኑ ልዩ ሁኔታዎች በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ፣ እንደገና ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ወይም ሊበሰብሱ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- ሞቅ ላሉ ወይም በመከደኛ ለተሸፈኑ ምግቦች መያዥያነት የሚውሉ መመጠኛ ስኒዎች ከየሲያትል ማዘጋጃ ቤት ሕግ (Seattle Municipal Code, SMC) 21.36.086 መስፈርቶች በጊዜያዊነት እንዲፈቀድላቸው ብቁ አይደሉም። ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ከ 3 ኢንች ዲያሜትር በታች የሆኑ መመጠኛ ስኒዎች ሊበሰብሱ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- ቡናማ ወረቀት የምግብ አገልግሎት መያዣዎች የሚፈቀዱት ሊበሰብሱ የሚችሉ ከሆነ ብቻ ነው።
- ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ አገልግሎት እቃዎች በግቢው ውስጥ ምግቡ ተበልቶ ሊበሰብሱ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
- ሊበሰብሱ የሚችሉ የምግብ አገልግሎት ዕቃዎች የተሻሻለውን የዋሽንግተን (Revised Code of Washington, RCW) ሕግ ምዕራፍ 70A.455 "የፕላስቲክ ምርት መበላሸት" መስፈርቶችን ማሟላት አለባቸው። በዚህ ህግ መሰረት ብስባሽ ምርቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው፡-
    - ሊበሰብሱ እንደሚችሉ ምርቶች በሶስተኛ ወገን የተረጋገጠ ወይም ሙሉ በሙሉ ከእንጨት ወይም ፋይበር ምንም የፕላስቲክ ሽፋን የሌለው መሆን አለበት።
    - ሊበሰብስ እንዲችል የተዘጋጀ እና በቀላሉ ሊለይየሚችሉ መሆን አለበት ማለትም

  "ሊበሰብሱ የሚችሉ" የሚለውን ቃል ማሳየትን ጨምሮ የኢንዱስትሪ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ምልክት እና ቀለም የሚያሳይ መሆን አለበት። በዚህ ሕግ ስር ያሉ መስፈርቶችን አስመልክቶ ዝርዝር መረጃ እዚህ (https://apps.ecology.wa.gov/publications/documents/2307022.pdf) ይገኛል።
- ለአንድ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ የምግብ-አገልግሎት ዕቃዎች በ RCW ምዕራፍ 70A.245.080፣ "አማራጭ አገልግሎት ዕቃዎች" መስፈርቶች መሰረት ማቅረብ አለባቸው። በዚህ ሀገር ህግ መሰረት ዕቃዎች፣ መምጠጫዎች (ስትሮዎች)፣ የማጣፈጫ ማሸጊያዎች እና ለቅዝቃዜ መጠጦች የሚሆን ኩባያ ክዳኖች በደንበኛው ጥያቄ ብቻ ወይም ራስን በራስ የማገልገል ማጠራቀሚያዎች ወይም ማከፋፈያዎች ሊቀርቡ ይችላሉ።

  በዚህ ሕግ ስር ያሉ መስፈርቶችን አስመልክቶ ዝርዝር መረጃ እዚህ (ecy.wa.gov/serviceware) ይገኛል።

የምግብ አገልግሎት ንግድ ሥራዎች የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይበረታታሉ፡-

- በሕክምና ወይም በአካላዊ ሁኔታዎች ምክንያት ደንበኞች በጠየቁ ጊዜ ለማቅረብ የሚታጠፍ ሊበሰብስ የሚችል የፕላስቲክ መምጠጫዎች (ስትሮዎች) ወይም የሚታጠፍ የፕላስቲክ መምጠጫዎች (ስትሮዎች) በቂ አቅርቦት መኖር፣ እና
- በተቻለ መጠን በግቢው ለሚበላው ምግብ ዘላቂ፣ በድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የምግብ አገልግሎት ዕቃዎችን እና ቁሶችን ያቅርቡ።

ለምግብ አገልግሎት የንግድ ሥራ በሚያስፈልጉት መስፈርቶች ላይ ተጨማሪ መረጃ የያዘ በራሪ ወረቀት አካትተናል።

የምግብ አገልግሎት ዕቃ መስፈርቶችን ሙሉ ዝርዝር ለማየት፣ እባክዎ የእኛን ድረ-ገጽ ይጎብኙ፡- bit.ly/spu-food-packaging

ነፃ መረጃዎችን እና ሙያዊ እገዛን ጨምሮ በSeattle የምግብ አስተሻሸግ ፕሮግራም ላይ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት እባክዎ በ 206-343-8505 ይደውሉልን ወይም በኢሜል greenbusiness@seattle.gov. ምላሽ ይፃፉልን

ከሰላምታ ጋር

Seattle Public Utilities Green Business
Program 206-343-8505
GreenBusiness@seattle.gov